የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ — የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 11
ADDIS ABABA – 15th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ..... ገጽ ፻፲፱
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................... ፻፳

## አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፹፰
## የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትአንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

· የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል ፤

"፩· ማንኛውም በከፍተኛ ወይም በአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ የተሰማራ ባለፈቃድ ግብር ከሚከፍልበት ገቢው ላይ ፴፭ ፐርሰንት የገቢ ግብር ይከፍላል ።"

፫· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## CONTENTS

Proclamation No. 23/1996
Mining Income Tax (Amendment) Proclamation ........................................ Page 119
Council of Ministers Regulations No. 3/1996
The Ethiopian Civil Service College Establishment Council of Ministers Regulations ............... Page 120

## PROCLAMATION NO. 23/1996
## A PROCLAMATION TO AMEND THE MINING INCOME TAX PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Mining Income Tax Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Mining Income Tax (Amendment) Proclamation No. 23/1996 "

2. *Amendment*

Sub-Article (1) of Article 3 of the Mining Income Tax Proclamation No. 53/1993 is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article (1):

"(1) A holder of large-scale or small-scale mining license shall pay 35 percent income tax on the taxable income."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 15th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February,1996

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፰
## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣ
## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· መቋቋም

፩· የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ "ኮሌጁ" ተብሎ የሚጠራ) እራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ኮሌጁ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል ።

፫· ዓላማ

ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፤

፩· የኢትዮጵያን ሕዝብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን በተለይ በክልሎች በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞችን በሥነ ጥበባትና በልዩ ልዩ ሙያዎች በማሰልጠን ኅብረተ ሰቡን በሚገባ ሊያገለግሉ የሚችሉበትን ሁኔታዎች መፍጠር ፤ ምልመላ ላይም ለሴቶችና ለኋላ ቀር ክልሎች ልዩ ግምት እንዲሰጥ ማድረግ፤

፪· ዕውቀት ማዳበር ፡ ማስፋፋትና ማስተላለፍ ፤

፫· ከዘር ፣ ከብሔር ፣ ከጾታ ፣ ከኃይማኖትና ፣ ከመሳሰሉት አድሎዎች ነጻ የሆነ በመከባበር ፣ በመተማመን ፣ በመተሳሰብና መቻቻል ላይ የተመሠረተና ሁለንተናዊ ስብዕናን የሚያበለጽግና የሰው ልጅ ክቡርነትን የሚያጠናክር ትምህርት መስጠት፤

፬· የሥራ ክቡርነትንና የኅብረተሰብን ብልጽግና የሚያራምድ አስተሳሰብ እንዲሰርጽ ማድረግ ፤

፭· በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች ሳይንሳዊ የሆነ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን ማሰራጨት ።

፬· ስለኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር

ኮሌጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· ፋክሊቲዎችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ክፍሎች ወይም ተቋሞች ማቋቋም ፤

፪· የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም መቀየስና ሥራ ላይ ማዋል፤

፫· የምስክር ወረቀት ፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ አካዳሚክ ሜዳይ ፣ ሽልማትና ማዕረግ መስጠት ፤

፬· ሴሚናሮች ፣ ወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀትና ማካሔድ ፤

፭· በሀገሪቱ ውስጥና በሌሎች ሀገሮች ከሚገኙ እቻ ተቋሞች ፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ጋር ግንኙነት መመስረት ፤

፮· የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ማቋቋምና ማሰራጨት፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO 3/1996
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN CIVIL SERVICE COLLEGE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the definition of powers and duties of the executive organs branch of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4 / 1995.

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

These regulations may be cited as the "The Ethiopian Civil Service College establishment Council of Ministers Regulations No. 3 /1996."

2. *Establishment*

1) The Ethiopian Civil Service College (herein after referred to as "the College") is hereby established as an autonomous higher education institution having its own legal personality.
2) The College shall be accountable to the Prime Minister.

3. *Objectives*

The College shall have the following objectives:

1) with a view to enhancing the Socio-economic development of the Ethiopian people especially to create conditions under which civil servants working in the Regions serve the people by training them in various skills and professions, to give special emphasis to women and backward regions in admission of students;
2) to search for, cultivate, preserve and transmit knowledge;
3) to provide education that fully develops the personality and strengthens the respect for human dignity, by promoting mutual respect, understanding, friendship and tolerance free from ethnic, nationality, sex, religious and other prejudices;
4) to inculcate the dignity of work and dedication for the well being of the society;
5) to conduct research and studies on different fields and disseminate fruitful results thereof.

4. *Power and Duties of the College*

The College shall have the following powers and duties:

1) to establish faculties and other academic and research units;
2) to design and implement undergraduate and graduate programmes;
3) to confer academic certificates, diplomas and degrees, as well as medals, prizes and titles for excellence and meritorious contributions;
4) to organize and conduct seminars, workshops and symposium;
5) to establish relations with domestic and foreign sister institutions, research institutions and other organizations having similar objectives;
6) to establish and publish academic journals and news letter

፯· የንብረት ባለቤት መሆን ፤
፰· ውል መዋዋል ፤
፱· በስሙ የመክሰስና የመከሰስ ፤
፲· ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባሮች ማከናወን ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለኮሌጁ የፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት

፭· ስለኮሌጁ ቦርድ መቋቋም

፩· ኮሌጁ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ሰባት አባላት ያሉት ቦርድ ይኖረዋል ፡፡
፪· ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል ፡፡

፮· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የኮሌጁን የአካዳሚክና የአስተዳደር አጠቃላይ ፖሊሲ ያወጣል፣ ይወስናል፤
፪· ኮሌጁ የሚተዳደርበትን ቻርተር አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል ፤
፫· የኮሌጁን አደረጃጀት ይወስናል ፤
፬· የኮሌጁን ም/ፕሬዚዳንቶች ሹመት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ ያስፀድቃል ፤
፭· የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያፀድቃል ፤
፮· በኮሌጁ በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማሩ የአካዳሚክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚ ተዳደሩበትን ሁኔታ ይወስናል ፤
፯· የኮሌጁን ዕቅድና ረቂቅ በጀት ያፀድቃል ፤
፰· የኮሌጁ መለያ ምልክት የሚሆነውን አርማ እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፤
፱· ኮሌጁ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች ይወስናል ፤
፲· ኮሌጁን በሚመለከት በማንኛውም የኮሌጁ አካል ወይም በኮሌጁ በተሰጠ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ግለሰብ የሚያቀር በውን አቤቱታ መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል ፤
፲፩· ኮሌጁ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የትምህርት ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን የአካዳሚክ ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል፤
፲፪· የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ፤
፲፫· የኮሌጁን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባ ሮችን ያከናውናል ፡፡

፯· የፋክሊቲ ካውንስል መቋቋም (ሴኔት)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የኮሌጁ ፋክሊቲ ካውንስል ይቋቋማል ፤

፩· የኮሌጁ ፕሬዚዳንት ............................ ሰብሳቢ
፪· የኮሌጁ ም/ፕሬዚዳንቶች ........................ አባል
፫· የፋክሊቲው ዲኖች ............................ ,,
፬· የኮሌጁ ሬጂስትራር ............................ ,,
፭· የተማሪዎች ዲን ............................ ,,
፮· ከኮሌጁ በቋሚ መምህራን ተመራጭ የሆኑ ሦስት መምህራን ............................ ,,
፯· በተማሪዎች የሚመረጥ አንድ የተማሪዎች ተወካይ ............................ ,,
፰· በፋክሊቲ ካውንስሉ የሚመረጥ ............. ፀሐፊ

፰· የፋክሊቲ ካውንስል ሥልጣንና ተግባር

የፋክሊቲ ካውንስሉ ተጠሪነቱ ለኮሌጁ ፕሬዚዳንት ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የኮሌጁን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል ፤

7) to own property;
8) to enter into contracts;
9) to sue and be sued in its ow. ıame;
10) to carry out other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

## PART TWO
## *Policy Making and Executive Organs of the College*

5. *Establishment of Board of Governors of the College*

1) The College shall have Board of Governors consisting of seven members appointed by the Prime Minister.
2) The Board shall have its own Secretary.

6. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to establish and determine the general academic and administrative policy of the College;
2) to get the charter of the College which regulates its administration drafted and submit it to the Government;
3) to determine the organization of the College;
4) to recommend to the Prime Minister nominees for the Vice-Presidents of the College;
5) to approve the rank of professors;
6) to determine conditions under which the teaching and research staff of the College shall be employed and administered;
7) to approve the plan and draft budget of the College;
8) to prepare the emblem of the College;
9) to fix and determine fees and charges to be paid to the College;
10) to inquire and decide any complaint concerning the College by any person with respect to a decision given by the College or any organ of it;
11) to approve academic agreements made by the College with domestic and foreign educational institutions;
12) to provide its own rules of procedure;
13) to perform such other duties as are conducive to the attainment of the objectives of the College.

7. *Establishment of the Faculty Council (Senate)*

A Faculty Council which consists the following members shall be established;

1) the President of the College ......... .......... Chairman
2) the Vice-Presidents of the College ............ Members
3) the Deans of the Faculties ...................... ,,
4) the Registrar of the College ...................... ,,
5) Dean of Students ...................... ,,
6) three teachers elected from the permanent academic staff ...................... ,,
7) A student representative elected by the students ...................... ,,
8) A secretary to be elected by the Faculty Council ...................... Secretary

8. *Powers and Duties of the Faculty Council*

The Faculty Council shall be accountable to the President of the College and subject to the general policy stated by the Board. The council shall have the following Powers and Duties:

1) examine and approve the academic calendar of the College:

፪· የኮሌጁን ልዩ ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ያፀድቃል ፤
፫· ዲግሪዎች እንዲሁም ሜዳይና ሽልማቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል ፤
፬· የተማሪዎች አቀባበልን ፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰንን ፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል ፣ በነዚሀ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል ፤
፭· አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥ ዘዴና ሁኔታን ይወስናል ፤
፮· የፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሀሣብ ያቀርባል ፣ ሌሎች የአካዳሚክ እድገቶችን ይወስናል ፤
፯· የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ፤
፰· በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

፱· <u>ስለ ኮሌጁ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንቶች ሹመትና ተጠሪነት</u>

፩· የኮሌጁ ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማል ፤ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል ።
፪· የኮሌጁ ም/ፕሬዚዳንቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮(፬) መሠረት ይሾማሉ ፣ ተጠሪነታቸውም ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል ።

፲· <u>ስለኮሌጁ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የኮሌጁ ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የኮሌጁን ሥራ በበላይነት ይመራል ፣ ያስተዳድራል ፣ ይቆጣጠራል ፤
፪· በቦርዱና በፋክሊቲ ካውንስሉ የሚሰጡ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል ፤
፫· በኮሌጁ በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማሩ የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፣ ደመወዝና አበላቸውን ይወስናል እንዲሁም የኮሌጁን የአስተዳደር ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ያስተዳድራል ፤
፬· የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ፤
፭· በቦርዱ ሲፈቀድ በኮሌጁ ስም የሚደረጉትን ማናቸውንም ስምምነቶችና የውል ሰነዶች ይፈርማል ፤
፮· በኮሌጁ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል ፣ ያንቀሳቅሳል ፤
፯· ኮሌጁን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል ፤
፰· በየሶስት ወሩ ስለ ኮሌጁ የሥራ እንቅስቃሴ ለቦርድ ሪፖርት ያቀርባል ፤
፱· በቦርዱና በፋክሊቲ ካውንስሉ የማሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል ።

፲፩ <u>ስለ ኮሌጁ ም/ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· የኮሌጁ ም/ፕሬዚዳንቶች ከኮሌጁ ፕሬዚዳንት በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩዋቸዋል ፤
ሀ) የኮሌጁን ሥራ በሚመለከት የኮሌጁን ፕሬዚዳንት ያማክራሉ ፣ ይረዳሉ ፤
ለ) ለነርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና በቦርዱና በፋክሊቲ ካውንስሉ የተሰጡ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላሉ ፣ ያረጋግጣሉ ፤
ሐ) ኮሌጁ የሚሰጣቸው ትምህርቶች በፋክሊቲ ካውንስሉ በፀደቀው የትምህርት ካሌንደርና የትምህርት ፕሮግራሞች መሠረት መካሄዳቸውን ይከታተላሉ ፣ ያረጋግጣሉ ፤

2) approve the College's various academic programmes;
3) decide on the conferring of degrees as well as medals and prizes;
4) formulate criteria for admission of students, determination of academic standards, settlement of disciplinary problems and to hear and decide complaints on these matters;
5) formulate guidlines for determining examination nature and methods;
6) recommend to the board the conferring of the rank of professorship and approve other promotions in academic rank;
7) issue its own rules of procedure;
8) perform such other duties as may be given to it by the board.

9. *Appointment and Accountablity of the President and the Vice-Presidents of the College.*

1. The President of the College who is accountable to the Board shall be appointed by the Prime Minister.
2. Vice–Presidents of the College who are accountable to the president shall be appointed pursuant to Article 6(4) of these regulations.

10. *Powers and Duties of the President of the College.*

The President of the College shall have the following powers and duties:

1) to guide, administer and control the activities of the College as a head;
2) to follow up and ensure the implementation of the decisions and directives of the Board and Faculty Council;
3) to employ and administer those engaged in teaching and research activities in the College in accordance with the directives issued by the Board; to fix their salary and allowance in addition to administer the administrative staff of the College in accordance with Civil Service Laws;
4) to submit to the Board the annual work programme and budget of the College for approval; to implement the same upon approval;
5) upon approval by the Board to sign all agreements and contractual documents entered into on behalf of the College;
6) to open and dispose bank accounts on behalf of the College;
7) to represent the College with third parties;
8) to submit reports to the Board on the activities of the College every three months;
9) to perform such other duties as may be given to him by the Board and the Faculty Council.

11. *Powers and Duties of the Vice–Presidents of the College.*

1) In accordance to the directives given by the President; the Vice-Presidents of the College shall have the following powers and duties:
   (a) to advice and support the President on the activities of the College;
   (b) to followup and ensure the implementation of decisions and directives given by departments accountable to them. by the Board and by the Faculty Council;
   (c) to followup and ensure the implementation of courses offered by the College according to the academic calendar and academic programme approved by the Faculty Council;

መ) በመማር ማስተማሩ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋሉ ፤
ሠ) በቦርዱ ፣ በፋክሊቲ ካውንስሉና በፕሬዚዳንቱ ተለይተው የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ ።

፪· የኮሌጁ ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ የኮሌጁ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ፕሬዚዳንቱን ተክቶ የኮሌጁን ሥራ ይመራል ፤ ያስተባብራል ።

፲፪· ስለ አካዳሚክ ኮሚሽን መቋቋም

እያንዳንዱ የትምህርት ፋክሊቲ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘና ተጠሪነቱ ለካውንስሉ የሆነ የራሱን የአካዳሚክ ኮሚሽን ያቋቁማል ፤

፩· የፋክሊቲው ዲን .............................. ሰብሳቢ
፪· የፋካልቲው ም/ዲን .............................. አባል
፫· የዲፓርትመንት ኃላፊዎች .............................. ”
፬· በፋክሊቲው ቋሚ መምህራን የተመረጡ ሦስት መምህራን .............................. ”
፭· ከሦስቱ የመምህራን ተወካዮች አንዱ ..... ፀሐፊ

፲፫· የአካዳሚክ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር

አካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የኮሌጁን የአካዳሚክ ፖሊሲ በመከተል የፋክሊቲውን የትምህርት ካሌንደርና የትምህርት ፕሮግራሞች ያዘጋጃል ፤ በፋክሊቲ ካውንስሉ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል ፤
፪· ለየትምህርት ዓመቱ በሚፀድቀው የትምህርት ካሌንደርና የትምህርት ፕሮግራሞች መሠረት በፋክሊቲው የሚሰጡ ፈተናዎችን ይወስናል ፤
፫· ትምህርታቸውን በሚገባ ላጠናቀቁ የፋክሊቲው ተማሪዎች ዲግሪ እንዲሰጥ ለፋክሊቲ ካውንስሉ ሃሣብ ያቀርባል ፤
፬· ወደሚቀጥለው የትምህርት እርከን የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ዝርዝር ለፋክሊቲ ካውንስሉ አቅርቦ ያስወስናል ፤
፭· ፋክሊቲውን የሚመለከቱ ማናቸውንም የአካዳሚክ ችግሮች መርምሮ ይወስናል ።

ክፍል ሦስት
ልዩ ልዩ

፲፬· የኮሌጁ ሌሎች አካላት

የኮሌጁ ልዩ ልዩ የትምህርትና የምርምር ክፍሎች የአመራር አካላት አመሠራረትና አሰራር በቦርዱ ይወሰናል ።

፲፭· በጀት

የኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል ፤

፩· ከፌዴራል መንግሥቱ ከሚመደብለት በጀት ፣
፪· ኮሌጁ ከሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ፤ እና
፫· ከሌሎች ምንጮች ።

፲፮· ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ።

(d) to provide assistances and services necessary for the teaching-learning process;
(e) to perform such other duties specifically given by the Board, by the Faculty Council and by the President.

2) The academic affairs Vice-President shall act as President in case of absence of the President He shall then direct and co-ordinate the activities of the College.

12. *Establishment of Academic Commission*

Each Faculty shall set up its own academic commission accountable to the Council which shall be composed of:

1) Dean of the Faculty .............................. Chairman
2) Vice-Dean of the Faculty .............................. Members
3) Department Heads .............................. ”
4) Three teachers elected by the permanent academic staff of the the Faculty .............................. ”
5) One of the three teachers representatives Secretary.

13. *Powers and Duties of the Academic Commission.*

The Academic Commission shall have the following powers and duties:

1) to prepare the academic calendar the academic programme of the faculty following the academic policy of the College; implement the same upon approval by the Faculty Council;
2) to determine the examination given by the faculty based upon the yearly academic calendar and academic programme;
3) to recommend to the Faculty Council students who have successfully complete their education and who shall receive a degree;
4) to forward to the Faculty Council for approval list of students who are going to be promoted to the next level;
5) to examine and decide academic problems concerning the faculty.

PART THREE
*Miscellaneous*

14. *Other Organs of the College*

The composition and functioning of organs of the various academic and research units of the College shall be determined by the Board.

15. *Budget*

The budget of the College shall be drawn from:

1) budgetary allocations by the Federal Government;
2) fees collected by the College; and
3) any other sources

16. *Inapplicable Laws*

Any regulations and directives inconsistent with the provisions of these Regulations shall not be applicable.

፲፯· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

17. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 1996

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE